*ወጣት ውብሸት ወልደሥላሲ በኢሕአፓ 36 ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ላይ ያሰማው መልእክት*

የተከበራችሁ የአሕአፓ ከፍተኛ አመራሮች፥ የአሕአፓን 36 ኛ ክብረ በዓል ለማክበር ከተለያዩ የአ ሜሪካ ከተሞች የተገኛችሁ የድርጅቱ አባላት፥ ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች እንዲሁም በዋሽንግተ ን ዲሲ በዓሉን ለማድመቅ የድርጀቱ ደጋፊና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በመሆን የተገኛችሁ እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ::

ይህ ድርጅት የዛሬ 36 ዓመት ህልም ቃጭል በነበረበት አመጽን ማደራጀት ቀርቶ ማሰብ ራሱ ወንጀ ል  ተብሎ በተፈረጀበት ግራ ቀኙ፥ ላይ ታቹ ጨልሞ ይቻላል ተራ ቃል ሳይሆን አደገኛና ለቅጣት ም የሚዳረግ ሆኖ በተገኘበትም... በዚያ ዘመን ነገንና የተነገ ወዲያን ብሩህ ኮከብ ከወዲሁ በተስፋ በ ማየት ሰፍኖ የነበረውን ሥርዓት ማቸነፍ ይቻላል ብለው ጨለማውን ለማስወገድ ክብሪት የጫሩ፥ .. . ዛሬም ላለው ሕዝባዊ ትግል ብርሃንን የፈነጠቁ በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ የትግል ቦታቸውን የሰ ጡ የአሕአፓ አባላት ምንጊዜም ህያው ሆነው የሚኖሩ በዚሁ በግንባር ቀደምትነት ለተደረገው የት ግል አስተዋጽኦ ምን ጊዜም የሚመሰገኑ ናቸው::  የድርጅት ዕድሜ ዓመት አልፎ አመት ሲተካ የ ሚደረግ ትረካ ሳይሆን ታሪክ በመንገዱ ያገኘውን እየጨፈለቀ ሲሄድ ይህ ድርጅት ኢሕአፓ ህልው ናውን ጠብቆ መከራ ሰቃዩን ተቋቁሞ ቃል ኪዳኑን ሳይክድ ዛሬም ድረስ ፀንቶ መቆሙንም አመላካች ነው::

ለዚህም ነው እኔ በዚህ ታሪካዊ ቀን በመገኘት ያለፉትን ለማውሳትና ለማወደስ ብቻ ሳይሆን ነፍስን .....ከእድሜና ጤና ጋር አድሏችሁ...የታገለቻሁና ያታገላችሁን በዚህ ቤት ዙሪያ ያላችሁትንም አባ ት እናቶቼ፥ ወንድም እህቶቼን ጭምር ለማሰብና ባደበባይ ቆሜ እናንተ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ጀ ግኖች ናችሁ ለማለትም ጭምር ነው:: ሆኖም ግን በዚህ ቀን ለድርጀቱ አመራሮችና ላገር ወዳድ ኢ ትዮጵያዊያን  ወገኖቼ ለመግለጽ የምፈልገው ዘወትር የመያሳስበኝና በሁሉም መድረክ ቦታ ባልተሰ ጠው ወጣቱ ትውልድ ላይ ነው:: ምናልባትም የኔም ህይወት ከእኒዘህ ወጣቶች ህይወት ጋር የተሳሰረ በመሆኑም ይሆናል:: ይህ ትወልድ ተረስቷል:: አስታዋሽ፥ አሳቢ ፥ ተቆርቋሪ አጥቷል::

የዛሬው የኢትዮጵያ ወጣት የተረሳ ትውልድ ሆኗል:: መሪ በጠፋበት አገር መሪ የሚመለመልበትና የ ሚፈለግበት ባህር ይህ ትውልድ ነበር:: ነውም:: ከእነዚህ መሃል ነበር ለአገራቸው መልካም ራዕይ ያ ላቸው ሰዎችን የነገ መሪዎችን የምናወጣው:: ትናንትን የሚያውቁ፥ ዛሬን የተረዱና ነገን በእርግጥ ትናንት ሳይሆን ነገ የሚያደርጉ ወጣቶችን ይህ ትውልድ ረስቷቸዋል:: የፖለቲካ ሥርዓቱ በጎሳ ጎራ ሲያሰልፋቸው የብሔራዊ አላማ ሲነሳቸው ይስተዋላል:: አንድ የአገር ዜጋ በሚያኮሩት የህገሩ ታሪኮ ች ይኮራል:: በሚያሳፈሩት ያፍራል:: የአንድ ሀገር ዜጋ መሆን ማለት አንዱና ዋነኛው መለያው ሀገ ር የሚለውን እውነት በውስጡ የተሸከመውን ታሪክ ልምድ ባህል እምነትና የመሳሰሉትን በሙሉ የ ራሱ አድርጎ የተለየ ክብር እና ክብደት በመስጠት ከሌሎች ሀገር ዜጎች ራሱን ለይቶ ማየትን የማያ ካትት ነው:: ዛሬ ትውልዱ ከዚህ እየራቀ የመጣ ይመስላል:: ድሮ በአገሩ ጭንቀት ጊዜ በጫካው በበ ረሃው ወዘተ.. ተሰማርቶ ዓለምን ባስደነቀ ሁኔታ ገድሎና ሞቶ ድል ያደርግ የነበረው ወጣቱ ነበር:: የዛሬው ወጣት አገሩ ነፃነትን፥ መጠነኛ መብትና ዴሞክራሲን ትንሽም ብትሆን የሕግ አገዛዝና የኢኮ ኖሚ ፍትህን ልታቀርብለት ስላልቻለችና ስለማትችል የአበበ በቢቂላን መንገድ መርጧል:: በይበል ጥ ወያኔ በሀገርም ሆነ በትውልድ ላይ ይቅር የማይባል በደልና ግፍ ፈጽሟል:: ወያኔ በትረ  ስልጣኑ ን በሀገሪቷ ውስጥ ሲያነግስ የተወለደ ልጅ በጥቂቱ ዛሬ 17 ዓመት ሆኖታል:: ከጡጦ ጋር የሚመገበ

ው ፕሮፓጋንዳ ነፍጥና ጠላት ... ወዘተ በሚሉ ቃላት ነው። ከርጥበት እድሜው ጀምሮ በጥላቻና በ ወገኑ የጠላትነት ስሜት ያደገው ህጻን ወደ ወጣትነት አፍላ ህይወት የሚሸጋገረው የዘረኛነትና የጎሳ ኝነት ወንጌል በቀጠረ  አፍ  ነው። የዚህን ወጣት ዕድሜ ከ10 ወይም ከ15 ዓመት በኋላ ስናየው የ22 እና የ30 ዓመት ወጣት ሆኖ እናገኘዋለን። ልንመልስ የምንፈልገው ጥያቄ ግን ይህ ወጣት ትውል ድ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ በአገር አምነት፥ በባህል ፥ ከሌሎች ወገኖች ጋር ተሳስሮ የመኖር፥ የጋራ ታሪኩን የመጠበቅና የማቆየት መንፈስ ወዘተ... በውስጡ አለወይ?ይኖረዋል ወይ? ነው ጥያቄው መ ልሱ አስፈሪ ነው የሚሆነው።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ ለብዙ ሺ ዘመናት የምትታወቀው ኢትዮጵያ አይደለችም። የአሁኗ ኢትዮጵያ አና ቷን ተቀልታ በታሪክ ያስጠራትን የንግድ የሥልጣኔ የጀግንነትና፥ የታሪክ፥ የባህር በሮችን አጥታ.. . በመላው አለም ማንነቷን ያስመሰከሩትን ሰሟን ያስጠሩትን የሥልጣኔ ምልክቶቿንና ቅርሶቿን ተዘ ረፋ... በኛ ያገር ተረካቢዎች ደካማነትና ኃላፊነት ያለመቀበል ጉድለት መላቅጧን አጥታለች። ዛሬ በአገር ውስጥ ያለው ወገን በጎረቤቱችግር ደንታ ቢስ ሆኗል። ጎጆው እየተቆረቆረ ካረፈባት መደብ ተጎትቶ የትም እስከሚጣል በስጋት ፥ በፍርሃት፥ በጭንቀት ተውጦ የነገውን የውድቀት እጣ ፋንታ እየተጠባበቀ ነው። በውጭ አለም የምንገኘው ወገንምከዚህ በባሰ ሁኔታ ይገኛል። አብዛኞቻችን ኢ ትዮጵያዊነታችንን ዘንግተናል። ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መሠረት አድርገን በተሰጠን የ ጥገኝነት ህይወት የመኩራራት አዝማሚያ እያሳየን ነው። ይህ ፍጹም ክብር አይደለም። ይህ ውርደ ት ማንነትን ማጣት ነው።

ያለፈው ደርግና ያሁኑ ወያኔ ትውልዱን በጥሩ መንፈስ ስላልኮተኮቷቸውና በኢትዮጵያ በረከት ቀም ሰው ለኢትዮጵያ መሞትን በውስጣቸው ስላልቀረጹባቸው የብሔራዊ አላማ ድሆች አድርገዋቸዋል። በትክክል ከተረዳነው ይህ ትውልድ ከክፉ የዘመናት መጋጠሚያ፥ ከአሳዛኝ ዘመንና ፥ የጠነዛ ፖሊ ተካ ወቅት ላይ ነው። ወያኔዎች ውሸት ዘርተው እውነት ለማምረት ...እጃቸውን በሌብነት ተግባር ዘርግተው አገር ለማስማማት ያላቸውን ዕቅድ ያወራሉ።--የፍትኅ ሚዛኑ የተሰበረበት የዳኝነት መንበ ር ዘርግተው የፖለቲካ ካድሬዎች ወርቃዊና ሰለሞናዊ ፍትሕ ሰጠን ይላሉ። ይህንን ፌዝ ለመዋጋት ይቻል ዘንድ ወጣቱን ትውልድ በትክክለኛ ሐዲድ አስገብተነዋልን? ይሄን በዘመናችን የተፈጠረውን አሳዛኝ ክስተት ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሃይማኖት አባቶች ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች ቸል ሳይሉና ሳይሰለቹ በጋራ መፍትሔዎችን የመፈለግ፥ አገርና ሕዝብን ከምንም በላይ በማስቀደም ከፍተኛ ሚና መጫወት አለባቸው። ይሄን እንደ ንስሀ ሁላችንም ልንመለከተው ይገባል።

አገራችን ኢትዮጵያ ትናንት የተፈጠረች መንደር አይደለችም። ከጊዜ በኋላ በጥቂት የፖለቲካ መሐ ንዲሶች የተቀነባበረች የጎጦች ግጥምጥሞሽም አይደለችም። ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለመፍጠር በሺ ህ የሚቆጠሩ ዘመናትን ጠይቋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕዝቦች ደም ፈሷል፥ አጥንታቸው ተከስክ ሷል። ይህ የኛ ክልል ነው፥ይህ ሰማችን ነው፥ ይህ መለያ ሰንደቅ ዓላማችን ነው ብለው የሕይወት መስዋእትነት ከፍለው ከቤተሰብ ስብስብ ከመንደርና ከጎጥ አልፈው የቋንቋን ድምበር ከሉዓላዊነት ግድብ ዘልቀው የትውልድን ህልውና ዋስትና አሸጋግረው አይተው አባቶቻችን በአገር ፍቅር ስሜት የመሠረቱልን አምባችን ናት። ያለፉትን አባትና እናት ጀግኖች የኢትዮጵያ ወላጆች ልንላቸው እን ችላለን። የወለዷቸው ልጆችስ ምን ዓይነት ናቸው? በጅምላ መናገር ስህተትም አልፎ ተርፎም ኃጢ አት ሊሆን እንደሚችል እገነዘባለሁ። ስለዚህ ጀግናም ወልደዋል፥ ብዙ እንከፍም አምጥተውብናል፥ ማለት ያዋጣል። በአብዛኛው በማኅበረሰባችን ውስጥ ሲዘዋወሩ የሚገኙትን በእሳት ልጅ አመድነት የተከሰቱን ግን ትርፍ አንጀት ትወልድ ሊባሉ የሚችሉት ናቸው። እዚህ ላይ ትዝ የሚለኝታላቁ ታ ጋይ ማህተመ ጋንዲ ነው። ጋንዲ የሕንድ አባት ተብሎ መጠቀስ ሲጀምር “ እኔ አባት ከሆንኩ ጠን ካራና ግዙፉን ልጆች እንዲኖሩኝ እመኛለሁ” ማለቱ ይጠቀሳል። የእያንዳንዳችን ጎጆ እንመርምርና

ለመሆኑ ማናችን ነን እንዲህ ያሉ ልጆች ወልደን ለኢትዮጵያና ለአምላክዋ ያሰረከበን? በርግጥ አን
ዲህ ዓይነት ልጆች ወልደው ያሳደጉ ሁሉ ብፁዓን ናቸው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ የጀግና ደሃ÷ የወጣት ታጋዮች ደሃ ናት ለማለት አይከጅለኝም፡፡ ዘወርወር ስል
ና ለትውልድ የውርስ ጉዳይ ስቆዝም ከአጠገቤ አንዳች ምርኩዝ ሳጣ ግን ምን ነካን? ምን ቀን መጣ?
ብዬ ሌላ ሰው ሳይሆን እራሴን እጠይቃለሁ፡፡ በረገፉት ወገኖቻችን እግር አያሌ አዳዲስ አበባዎች ለ
ማየት አይኖቼ ሲራቡ ነውኢትዮጵያ ምን ይበጃት ይሆን? ብዬ የማሰላስለው፡፡ የአእምሮ ልፍስፍሶች
በአጠገቤ ሳይ ይህ ጭንቀት ያንገላታኛል፡፡ እንደማምነው ይህ ጭንቀት የሁላችንም ጭንቀት ነው፡፡
ኢትዮጵያ ለወጣቶቿ የምትሰጠው ፀጋ በመጥፋቱ የሚሞትላትና የሚኖርላት ወጣት ዜጋ አጣችን?
የሚል የማልመልሰው ጥያቄ ይመጣብኛል፡፡ የችግሩንባህር ቀዝፎ የሚያልፍና የሚያስለፈን ጠፉ ብ
ዬ ስጠይቅ ግዙፉን ድርጅት አስባለሁ፤ ኢሕአፓን ማለቴ ነው፡

ይህ ድርጅት ለኢትዮጵያ ነፃነትን ለሕዝቦች አኩልነትን መብትን በሀገሪቷ ውስጥ ለማምጣት በተደረ
ገው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከፈተኛ ሚናዎችን ተጫወቷል፡፡ ዛሬም በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚያ
የትናንት ወጣቶች የሀገራችን ነፃነት መሥራች አባቶችና እናቶች ወደ ትግሉ መድረክ ሰገቡ ለራሳቸ
ውም ሆነ ላሁኑ ትውልድ ሰፊ አሳብና ግዙፍ ተስፋ የነበራቸው ሰዎች ነበሩ፡፡ የትናንት ታጋዮቻችን
እና ዛሬም እድሜ አግኝታችሁ በህይወት ላላችሁ የኢሕአፓ ጓዶቻችን የትግል እርማችሁን አንስተን
ላለነው የዛሬው ወጣቶች የክብርና የኩራት ምንጫችን ናችሁ፡፡ እናንት በደምና ባጥንታችሁ ያቀለ
ማችሁትን ትግል ዛሬ የናንተን አደራ አንስተን ለጀመርነው ሕዝባዊ ትግል በመንፈሳዊና ስጋዊ ህይ
ወት ያላ ጥንካሬን ለብሔራዊ እርማነት ዘብ መቆምን ያወረሳችሁት ሀገራዊ ሀብት በመሆኑ በሀገር
ውስጥም ሆነ በወጭው ያለን ወጣት ልጆቻችሁ እንኮራባችኋለን፡፡ ዛሬም በዚበህ ታሪካዊው ቀን እን
ድገኝ ወክለው በላኩኝ የኢትጵያ ወጣቶች እና የናንተን የትግል ችቦ ለኳሾች ስም ይህ ድርጅት-ኢ
ሕአፓ- ለሚሰጠን ማንኛውም ሀገራዊ ትግል ዛሬም እንደትናንቱ ከጎናችሁ ለመሰለፍ ቃል እንገባለን
እላለሁ፡፡

አንዳንድ ሰዎች የፖለቲካ ግንዛቤ የሌላቸው ሆኖም ግን እውቀታችሁስ ቢባሉ እድሚያቸውን መቁ
ጠር ብቻ የሚፈልጉ ሰዎች ይህ ድርጅት -ኢሕአፓን- ዕድሜ ብቻ ነው የያዘው በማለት ለማንቋሸሽ
ሲሞክሩ ይስተዋላል፡፡ በርግጥ ይህን እንደምርቃት ነው የማየው፡፡ ባገራችንም ዕድሜ ይስጥህ ይባላ
ል ፡፡ ዕድሜ ብዙ ያሳያልና ነው፡፡ ዛሬ ይኸው ዕድሜ ሰጥቶት 36 ኛ ዓመቱን ያስከብራል፡፡ ይኸው ዛ
ሬ ከምንጊዜውም በላይ እርማውን ባነሱና ትግሉን በሁሉም አቅጣጫ ለማቀጣጠል በተዘጋጁ ወጣቶ
ች መከበቡ የድርጅቱን ጥንካሬና የፖለቲካ አካሄዱን ብቃት ያሳያል፡፡

ዛሬ ወያኔ ወጣቱን ተስፋ ያጣና የመከነ ትውልድ ለማድረግ ሀገራዊ ራዕያችን በጎሳ እምነትና ታሪካ
ችንን በቀበሌና በመንደር ገድቦ በኢትዮጵያዊነት የዘመተ ኃይል ስለሆነ እኛ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች
በማንኛውም ጉዳይ ላይ ተሳተፏችንን በማጠናከር ወያኔን በቁርጠኝነት ከሚታገሉ ኃይሎች ጎን መቆ
ም አለብን፡፡ በ1966 የኢትዮጵያ ወጣቶች የከፈሉት መስዋእትነት ጊዜና ወቀት የማይሽረው ሐቅ ነ
ው፡፡ በመሆኑም አገራችን እንዲህ ያለ ፈታኝ እና መስቀለኛ መንገድ ላይ ባለችበት ወቅት እኛ ወጣ
ቶች ለሀገራችን እና ለሕዝባችን ነፃነት መታገል ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ግዴታችን ነው፡፡

ያሁኑ ዘመን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ስንባል መኖር የበደለን ያልታደልን ፍጡሮች ብንሆንም የሰ
ው ምርትአልቆ በግርዱ ዘመን ላይ አይደለምና የደረስነው ሀገራችን ላለችበት ብሔራዊ ቀውስ እን
ደትናንት ወንድም እህቶቻችን የዛሬው ወጣቶች በማንኛውም መንገድና መስክ ትግሉ የሚጠይቀው
ን ማበርከት ብሔራዊ ግዴታችን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ክብርም ጭምር ነው እላለሁ፡፡ ኢትዮጵ
ያ ሀገር የምትሆንበትን ቀን እናፍቃለሁ፡፡ አመሰግናለሁ